# ውስጠ ዴሞክራሲያዊ ነጻነት እጦት የወለደው
# የአመራር አባሉ  ኑዛዜ

**ዮናስ**  04/26/13

የአንድነቱ ስራ አስፈፃሚ አባልና የድርጅት ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የሆኑት ኢንጂነር ዘለቀ ረዲ ሚያዚያ 9/2005 ዓ.ም ለሠንደቅ ጋዜጣ የሰጡትን ድርጅታዊ ኑዛዜና ማጋለጥ ቀጥለው ሚያዝያ 15/2005 ዓ.ም ደግሞ ኢትዮ ምህዳር በተሰኘው ጋዜጣም ደግመውታል፡፡

ጉዳዩ እንዲህ ነው፡- የአንድነት ፓርቲ አመራሮች አምባገነኖች በመሆናቸው እና በነፃነት ሊያሰሯቸው ባለመቻላቸው ፓርቲውን በገዛ ፈቃዳቸው የለቀቁ መሆኑን የሚገልፀው የኢንጂነር ዘለቀ ረዲ የኑዛዜ መግቢያ ቢሮ ውስጥ ያሉት የአንድነት አመራሮች ደመወዛቸው እንዲጎድልባቸው እንደማይፈልጉና በፓርቲው ውስጥ ግልጽ የሆነ የፋይናንስ ስርዓት ባለመኖሩ ለትግሉ ሳይሆን ለጽ/ቤቱ የሚወጣው ገንዘብ ሞቅ ያለ ነው  ይላሉ።

በተለይ የጽ/ቤቱ ሃላፊ አቶ አስራት ጣሴ በአብዛኛው ለሥራ ማከናወኛ ገንዘብ እንዲወጣ እንደማይፈልጉ እና ከዲያስፖራ የሚላክ ገንዘብ ቢኖርም እኔ እንደ አንድ የስራ አስፈፃሚ አባል የተሟላ መረጃ እንዲኖረኝ እንኳ አይፈልጉም ብለዋል። በሠንደቅ ጋዜጣ ላይ የሰፈረው የአንድነት ፓርቲው ከፍተኛ አመራር ምስክርነት እንደሚጠቁመው በተለይ አቶ አስራት የዘረጉት ቢሮክራሲ የማያሠራና የድርጅቱም ገንዘብ አሳማኝ ባልሆነ ስራ ላይ እንደሚውል ያጋልጣል፡፡

የአንድነት ፓርቲ ሊቀመንበር የሆኑት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ሲበዛ ግልፍተኛ መሆናቸውን የሚገልጹት ኢንጂነር ዘለቀ  ዶ/ሩ ከኢህአዴግ የወጡት በግልፍተኝነታቸው እንጂ አስበውበት እንዳልሆነና ዴሞክራሲያዊ የግል ባህሪ እንደሌላቸውም አመልክተዋል፡፡ ዶ/ር ነጋሶ ተቃዋሚ ፓርቲን ከተቀላቀሉ ጀምሮ አንድም ያፈሩት ተተኪ ወጣት አመራር እንደሌለና አቶ አስራትም በተመሳሳይ ወጣት ማብቃት እንዳልቻሉ በመጥቀስ የወደፊቱ የወጣቱ ፈተና እነዚህን አዛውንቶች ዴሞክራሲ ማስተማር እንደሆነም አውስተዋል፡፡

የአንድነት ፓርቲ የፋይናንስ ኮሚቴ የ2004 ዓ.ም ለአንድነት ፓርቲ ማጠናከሪያ የገቢ ማሰባሰቢያ የእራት ፕሮግራም ትኬት ሽያጭ በአግባቡ ገቢ እንዳልተደረገ ምንጭ ጠቅሶ ያሰፈረው ይህ ዘገባ በውስጠ ዴሞክራሲያዊ እጦት ለሚታመሰው አንድነትና መሰል ፓርቲዎች ቀጥዬ ለማነሳው ሃሳብ ጠቃሚ ሆኖ አግኝቸዋለሁ፡፡

በተመሳሳይም የአንድነት ፓርቲ ድርጅት ጉዳይ ሃላፊ ኢንጂነር ዘለቀ ረዲ በኢትዮ-ምህዳር ጋዜጣ ላይ ያሰፈሩትን ሃሳብ ስንመለከት ስለታቀዋሚ ፓርቲዎች ውስጠ ዴሞክራሲያዊ እጦትና ትርምስ ግልጽ የሆኑ መረጃዎችን እናገኛለን፡፡

ኢንጂነር ዘለቀ የምወደውና የማከብረው ስለሚሉት የአንድነት ፓርቲ ሲያብራሩ የፓርቲውን ህልው መሆን ተጠራጥረው እና እየጎመዘዛቸው ነው፡፡ የአንድነት ፓርቲ ላዕላይ ም/ቤት የሚባለው ከፍተኛ ምክር ቤት ስብሰባ አድርጓል" በሚል ከሰፈረው ነጥብ የተሰመረበት ቃል ለፓርቲያቸው ያላቸውን ታማኝነትና ስለፓርቲያቸው ያላቸውን አቋም እምን ድረስ እንደሆነ የሚያመለክት ነው፡፡በፓርቲው ውስጥ የዴሞክራሲ ባህል እንደሌለና ዝም ብሎ ስለሊበራል ዴሞክራሲ መዘመር እንጂ በሊበራል ዴሞክራሲ ውስጥ የሚሰሩ ሥራዎችና የሊበራል ዴሞክራሲ መገለጫ የሚሆን ባህል እንደሌለ ለኢትዮ-ምህዳር የተናገሩት ኢ/ር ይልቃል በማሳያነትም ራሳቸውን በተመለከተ አንድ ጋዜጠኛ" ለፓርቲው ዋና ፀሃፊ አቶ አስራት ጣሴ እንጂነር ዘለቀ ጥሩ ሥራ እየሰራ ነው በሚል ለሰጣቸው አዎንታዊ አስተያየት እባክህ ተወው ኢህአዴግ እየሰበሰበብን ነው" ብለው መናገራቸውን በማቅረብ በትክክለኛነት በአባልነት ኢህአዴግን እያገለገለ ያለው ማነው ብሎ ቢፈተሽ ከአቶ አስራት ጣሴ ኪስ የኢህአዴግ መታወቂያ እንደሚገኝ አስፍረዋል፡፡

ሃሳቤን በጋዜጣ በመግለጼ አቶ አስራትን እና ዶ/ር ነጋሶን ነክተሃል በሚል በዲሲፒሊን ጉድለት እንደተጠየቁ የገለጹት ኢ/ር ዘለቀ በድርጅት ጉዳይ ላሳዩት አፈጻጸም "D" የሰጧቸው የአንድነት ፓርቲ ሊቀመንበር ዶ/ር ነጋሶ ለድርጅት ስራ ብለው 100 ብር አዋጥተው እንደማያውቁና የፓርቲው ዋና ፀሃፊ የሆኑት አቶ አስሥራት ጣሴ ለድርጅት ጉዳይ ገንዘብ ሊሰጡ ይቅርና ከቻሉ እንደሚቀሙ የውስጠ አዋቂነት ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል፡፡

ኢህአዴግን በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ከፋፋይና የከፋፍለህ ግዛ ባላባት እንደሆነ ሲጽፉና ሲናገሩ የማይደክሙት የአንድነት ፓርቲ ከፍተኛ አመራሮች ዋና ከፋፋይና የከፋፍለህ ግዛ መርሆ አራማጅ ስለመሆናቸውና ክፍፍሉን የሚፈጥሩትም አቶ አሥራት ጣሴ ናቸው በሚል ከቀረበው የኢ/ር ዘለቀ ምስክርነት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ አንድ ሰው የሆነ ነገር አድርጓል ካሏቸው ተናጋሪው መረጃውን ከአፉ ሳይጨርስ ከተባለው ሰውዬ ጋር ይጋጫሉ በሚል ስለዶ/ር ነጋሶ በራሳቸው መቆም አለመቻል አብራርተዋል።

በኢትዮ-ምህዳር ጋዜጣ ላይ የሰፈረውና አስገራሚው ነጥብ ደግሞ ሃሳብን በነፃነት በጋዜጣ በመግለጼ እነ ዶ/ር ነጋሶና አቶ አሥራት ጣሴ አቶ ጁነዲን ሳዶን እንደምሳሌ በማንሳት "እንደሱ በኢህአዴግ መከራ የደረሰበት እንደሌለና ነገር ግን የፓርቲው ዲሲፒሊን ስለሆነ ስለፓርቲው አልተናገረም" መባላቸው እንደሆነ ገልጸው በአንድነት ፓርቲ ውስጥ ሃሳቡን በነፃነት የሚገልጽ ማንኛውም አባል

ከፍተኛ አመራሮቹ የስልጣን እድሜያቸውን ለማራዘም ሲሉ ፓርቲውን ለማፍረስ የተሰጠ የአፍራሽነት አስተያየት ነው በማለት እንደሚያሽማቅቋቸውም አውስተዋል፡፡

የብቃት ማነስ ስለሚታይበት አብረን መሥራት አልቻልንም" የሚሉና መሰል ይዘት ላላቸው የኢንጂነር ዘለቀ ክሶች ምላሽ በፓርቲው ሊቀመንበር ዶ/ር ነጋሶ ቢሰጥም በመርህ የለሽ ተቃውሞና ውስጠ ዴሞክራሲያዊ እጦትና በለምን ተነካሁ ባይ ግልፍተኛ ስሜት በመነዳት ከምርጫ ጉዳይ ጋር በማያያዝ በኢትዮ-ምህዳር ጋዜጣ ላይ የተውገረገረ ሀሳብ ቀርቦ ተመልክተናል።

ኢንጂነር ዘለቀ በራሳቸው ፈቃድ ሳይሆን በአቅም ማነስ ችግር የአንድነት ፓርቲ አመራሮች እንዳሰናበታቸው ድርጅቱ ገልጿል። ኢንጂነር ዘለቀ ረዲ በራሳቸው ፈቃድም ይሁን በአቅም ማነስ ብቻ ከአንድነት ፓርቲ ሥራ አስፈጻሚነት መልቀቃቸው ወይ መባረራቸው እርግጥ ሆኗል። ይህ ባለበት ሁኔታ "ምርጫና አማራጭ የሌላት ሀገር" የሚለው መጣጥፋቸው "ይውጋህ ብሎ ይማርህ" ዓይነት ነገር ነው የሆነብኝ።

ኢንጂነር ዘለቀ እነ አቶ አሥራት ጣሴንና ዶ/ር ነጋሶን ለመንቆር በፈለጉበት በዚህ ሰዓት ያን ሲያጥላሉት የነበረውን ኢህአዴግና አመራሩን ለማድነቅ ፈለጉ፡፡ ፈለጉናም አልቀሩ የቦረና ህዝብ ለስራ በሄድንበት ጊዜ "ከሊቅ እስከ ደቂቅ ወጥቶ ተቀበለን" ብለው የአካባቢው አመራሮች ገና ወጣቶች መሆናቸውንም በመጥቀስ አድንቀዋል፡፡ ግን ደግሞ ልባቸው አንድነት ቤት ነበርና ደነገጡ። ስለደነገጡም የኢህአዴግ አመራር የሆኑት ወጣቶችን ወይም የአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ፍልስፍና መስመርተኛ የሆኑትን ወጣቶች የገዳ ሥርአት ፍሬዎች ናቸው በማለት ከኢህአዴግ ለማራቅ ሙከራ አደረጉ ።

|አንዳንድ የሃገራችን ተቃዋሚዎች ቦረና ሄደው ስልጠና ቢወስዱ እንዴት ጥሩ ነበር። ወጣቱን ለማየት የማይፈልጉ አመራሮቻችን ቢጠየቁ፣ ለቦረና ህዝብ ሁሉ እንደሚታገሉ ሊያወሩ ይችሉ ይሆናል´ የሚሉን ኢ/ር ዘለቀ አንዳንድ የሃገሬ ተቃዋሚ ከማለት አቶ አስራትና ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ቢሉን በተሻለን በነበር። ምን ይህ ብቻ የሃገሬ ተቃዋሚዎችን ውስጠ ዴሞክራሲያዊ ነጻነት እጦትና ትርምስ እርሶ ሲባረሩ ነው የታይዎት ወይ? ብለንም እንጠይቃቸዋለን። እርሶ ከእነርሱ እንደማይሻሉ ለመገመት አስችሎናል ብለንም እንነግራቸዋለን።

ሳይደግስ አይጣላ እንዲሉ የኢንጂነር ዘለቀ መባረር ሌላም ጉድ ይዞልን እንዲመጣ አድርጓል። ከተጠናቀቀ ሳምንት ያልሞላውን የአዲስ አበባና የአካባቢ ምርጫ በተመለከተ 33 ፓርቲዎችን የማስተባበር ሃላፊነት ወስዶ እና የአንሳተፍም አድማ አስመትቶ የነበረው አንድነት ፓርቲና የድርጅት ጉዳይ ሃላፊያቸው በምርጫው ላለመሳተፍ ያስቻሉን ምክንያቶች ሲሉ ብዙ ብዙ ነገር ማለታቸው የቅርብ ቀን ትዝታ ነው።

ታዲያ ዛሬ ሳይደግስ ላይጣላ ይህን አድማና ፀረ ዴሞክራሲያዊ ፖለቲካ ግልጥልጥ አድርገውልን እርፍ ማለታቸው የሚያስጠይቀውና የሚያስገምተው ዶ/ር ነጋሶና አቶ አስራት ጣሴን መስሏቸው ከሆነ ኢ/ር ዘለቀ "ተሸውደዋል።" የድርጅት ጉዳይ ሃላፊ እንደመሆናቸው በዋናነት የምንታዘበውና የምናቀለው በዋናነት ኢንጂነር ዘለቀን ስለሆነ።

ለመገመቱም ለመታዘቡም በኢንጂነር ዘለቀ ኑዛዜ ምርጫውን በተመለከተ ከሰፈሩት ነጥቦች ጥቂቶቹን እንመለከት። በእርግጥ በዘንድሮው የተቃዋሚ ፓርቲዎች አለመሳተፍ የራሳቸው የአመራሮቹ ችግር እንጂ የገዢው ፓርቲ  አይደለም። ድል የሚገኘው ጫና በመፍጠር ነው የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች እንዲስተካከልላቸው አንዳንድ ነገር ጠይቀው እርሱ እስካልተመለሰ ድረስ በምርጫው አንሳተፍም አሉ ፤ በዚህ እለት ህዝቡ አማራጭ አጣ ማለት ነው። የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎቹ ኢህአዴግ እንዲያነጋግራቸው በተደጋጋሚ ሲጠይቁ ይሰማል። በምርጫ ሊደርስባቸው የሚችለውን ጫና ትቶ ምርጫው ሰላማዊ እንዲሆን የሚል ተጽእኖ ሲያቀርቡ ይሰማል። ይህ አይነቱ መብት ግን በእጃቸው የነበረ ሲሆን ያንን መብታቸውን መጠቀም ሳይፈልጉ፣ ኢህአዴግ እንዲሰጣቸው የመፈለግ አባዜ ተፀናውቷቸዋል። ሁልጊዜ የእንደራደር ወረቀት መጻፍና ያደራድሩናል ብለው የሚያስቧቸውን ዲፕሎማቶች ደጅ መጥናት፣ ዋና ተግባር አድርገው በመያዛቸው ህዝቡን አማራጭ በማሳጣት ኢህአዴግ ያለከልካይ እንደፈለገ እንዲሆንበት አድርገዋል።"

ኢንጂነር ዘለቀ ምርጫው የተከናወነው ሚያዚያ 6/2005 ዓ.ም እርስዎ ከአንድነት ፓርቲ ከፍተኛ ስራ አስፈፃሚነት የተነሱት እንደ ዶክተር ነጋሶ ገለፃ ሚያዚያ 12/2005፤ ታዲያ ከላይ የተቃዋሚ ፓርቲዎችን በተመለከተ የዘረዘሯቸው አባዜዎች ሁሉ እርስዎንም እንደሚመለከቱና እንደውም በዋናነት እርስዎ የሚገለጹባቸው ነጥቦች መሆናቸውን ስለምን ዘነጉት?። ከደሙ ንፁህ ነኝ ብሎ መታጠብስ በምን አግባብ ይቻል ይሆን? ይህቺን ይህቺን ለማያውቁት ቢነግሯቸው ጥሩ ነው።

ኢንጂነር ዘለቀ ሲቀጥሉ |አንዳንድ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች፣ ሚዲያ ከነቀፋቸው የገዢው ፓርቲ ደጋፊ ስለሆነ ነው ሲሉ ግለሰብ ከሆነ የገዢው ፓርቲ ተላላኪ ይሉታል´ ይሉናል ። መቼም በጋዜጣ መፃፍና ነቀፋ የተጀመረው ከሚያዚያ 9/2005 በኋላ አይደለም። ስለሆነም እርስዎ በሰንደቅ ጋዜጣ ላይ ኑዛዜዎን ሚያዚያ 9 ከማስፈርዎ በፊት የፃፏቸውን ጽሁፎች ዞር ብለው ቢመለከቷቸው የፃፈውንና የተቸውን ሁሉ በዋናነት "የኢህአዴግ ተላላኪ እና ተለጣፊ" ሲሉ የነበሩት እርስዎ መሆንዎን ያውቁታል። ዛሬ ስለተባረሩ "አንዳንድ" በማለት በሁለት ግለሰቦች ላይ ለማላከክና በቂም በቀል ስሜትዎን ለመተንፈስ ባይሞክሩ ጥሩ በነበር። ግን ደግሞ ጥሩ የሚሆነው ለአንድነትና ለተቃዋሚዎቹ መንደር ነው። እኛማ ከምርጫ 97 በኋላ አወቅናችሁ በቃችሁን ብለን አርፈን ተቀምጠናልና አዲስ ነገር ሊሆኖብን አይችልም።

ተቃዋሚዎች ስኬትን በልመና እና በሽምግልና ለመቀበል መሞከራቸው ለስልጣን ያላቸውን ጉጉትና ጥማት የሚያመለክት ነው የሚሉት ኢንጂነር ዘለቀ እሳቸው አይመለከተኝም ቢሉም በዋናነት እራሳቸውን የሚመለከትና ለሌሎቹም ተቃዋሚ ሃይሎች ባስተላለፉት የኑዛዜ ማሳረጊያ እኔም ልሰናበት። ውድ የተቃዋሚ መሪዎች ሰርቶ መገኘት እንጂ በአጉል እንቶ ፈንቶ ራስን ወጥሮ መታዬት የትም አያደርስም። እኛም እኮ ተቃዋሚ ፓርቲዎች አብዛኛውን ጊዜ ከምርጫ ሊወጡ የሚሞክሩት የራሳቸውን ዝሆን የሚያህል ድክመት በመሸፈን በትናንሽና ሰንካላ ምክንያት ነው ብለን ነበር እክ ኢንጂኒየር።